Verein der Amhara in Deutschland(VAD) e.V.
Espenstraße 60
65933 Frankfurt am Main

የአማራ ማኅበር በጀርመን
The Amhara Association in Germany
vad.amhara@gmail.com
Twitter: @VADeutschland

17.07.2023

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ : ከሐዋርያነት ወደ ጎሳዊ ፋሽስቶች አገልጋይነት!

በፋሽስት አገዛዝ ሥር በወደቁ አገራት፣ቤተእምነቶች ሳይቀሩ የፋሽስታዊ ፖለቲካ አራማጆች እንደሚሆኑ የናዚ ጀርመን ታሪክ ያሳየናል። ዛሬ የእነ አብይ ኦሮሙማና የትግራይ ጎሣዊ ፋሽስቶች ቤተእምነቶችን የተቆጣጠሩበት መንገድ ከናዚዎቹ ጋር አንድ ነው። በዚች ፅሑፍ መጨረሻ ላይ የናዚዎቹን መንገድ በአጭሩ እንገልፀዋለን። መጀመሪያ ግን ለትግራይ „እምነት አባቶች" አንድ ሁለት ነገሮችን እንበል ።
የትግራይ „የእምነት አባቶች" በወልቃይት ጠለምትና ራያ አማሮች ላይ ለ27 ዓመታት ትሕነግ የፈፀመውን አሰቃቂ ወንጀል በዝምታ በማለፍ ተባብረዋል ። በ2014 ዓም በትሕነግ መሪነት የትግራይ ልሂቆች አማራውን ሲወሩ የትግራይ „የእምነት አባቶች" በአማራው ላይ ሂሳብ እናወራርዳለን የተባለውን የልጆቻቸውን አሰቃቂና አሳፋሪ ድርጊት በለሆሳስ በመደገፍ ዝምታን መርጠዋል። በዚህ ወረራ እናቶችና ታዳጊ ልጆች በወራሪው ኃይል ተደፍረዋል፣ ስፍር ቊጥር የሌላው ንጹሃን አማራ ተጨፍጭፏል፤ በሽዎች የሚቆጠሩ ት/ቤቶችንና የጤና መገልገያዎች ወድመዋል፤ የደሃው አማራ ሐብት ሊጥ ሳይቀር ተዘርፏል። ይሄ ወረራና ዘረፋ በገንዘብ ሲተመን ከ300 ቢልየን ብር ይበልጣል ። በመሆኑም „የትግራይ የእምነት አባቶች" በዝምታ ተባባሪነታቸው የሲኦሉንም ጉዞ ከጀመሩ ውለው አድረዋል ። የትግሬ ጎሠኛነታቸው ስለበለጠባቸው ይሄን የአማራ ጭፍጨፋ ማንሳት አይፈልጉም ። ስለዚህ እነዚህ „አባቶች" እንኳን ይቅርታ ሊጠየቁ ቀርቶ ፣ በእግዚአብሔር ፊት፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ጊዜው ሲደርስ በሕግም ይጠየቃሉ።

ሐምሌ 2 ቀን 2015 ዓም የሲኖዶሱ ተወካዮች(አማራ ጳጳሶችም ነበሩበት!) „ይቅርታ" ለመጠየቅ መቀሌ በተገኙበት ጊዜ አንድ የትሕነግ ካድሬ ከፊታቸው ቆሞ ፋሻስታዊ ፕሮፓጋንዳውን እንደ በረዶ አወረደባቸው። የሚደንቀው የአማራ ጳጳሶች ዝም ማለታቸው ነው። ምናልባት እንደ ብርሃኑ ነጋ „ለኢትዮጵያ ነው የቆምነው" ብለው ይሆናል። ሐምሌ 5 ቀን 2015 ዓም ፓትርያርኩ የገንዘብ እርዳታቸውን ለማስረከብ መቀሌ ሲገኙ የተቀበለው የጀኖሳይድ ወንጀለኛው ጌታቸው ረዳ እንጂ ከትግራይ አባቶች የተገኘ አላየንም ። ፓትርያርኩ ከነተከታዮቻቸው ጸሎት ለማድረግ ወደ ቤተክርስቲያን ቢሄዱም የቤተክርስቲያኗ በር ሳይከፈትላቸው በመቅረቱ ፀሎታቸውን ደጃፍ ላይ አድርገው ከውጭ ተመልሰዋል ። ለመሆኑ እነዚህ ካድሬ „አባቶች" ቤተክርስቲያኗ ውስጥ ምን ደብቀው ይሆን ፓትርያርኩን አናስገባም ማለታቸው? ምንም ቢሆን ፓትርያርኩ በ2014 አንድ ትግሬ ቤንሻንጉል ውስጥ እሳት ውስጥ ተወርውሮ በመቃጠሉ ስቅስቅ ብለው አልቅሰዋል። እንኳን ፓትርያርኩ በወለጋ፣ በጅማ እርጉዝ አማራ እናቶች ሆዳቸው ተዘርግፎ እንደተገደሉ ያልሰሙ! ! ተንሰቅስቀው ይሞቱ ነበር።

የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከተመሰረተችበት ከ2000 ዓመታት በፊት ጀምሮ እስከ ዛሬ ቀኖናውንና ዶግማውን በማክበር ኖራለች። በየወቅቱ የተጋረጠባትን አደጋ ታግላ በማሸነፍ እዚህ ደርሳለች ። የግራኝ አህመድ ወረራንና ተከትሎ የመጣውን የ16ኛው ክፍለ ዘመን የጋላ ወረራን አልፋ ህልውናዋን በማስከበር ተሻግራዋለች። የአብይ አህመድንና የትህንግ ጎሳዊ ፋሽስቶች ከእነ አገልጋዮቻቸው የጫኑባትን የዘረኝነት ትቢያ አራግፋ እንድትቀጥል የምእመናኑና የእውነተኛ ኦርቶዶክስ አባቶች መራራ ትግል አይቀሬ ሆኗል። በአቡነ ማትያስ የሚመራው ሲኖዶስ ፣ በፍራቻም ይሁን በምድራዊ ጥቅም ተይዞ ቀኖናውን በመሻር የጎሣዊ ፋሽስቶችን ፖለቲካ እየፈፀመ ነው።

በአሁኑ ጊዜ ቤተክርስቲያናችን እዚህ አጣብቂኝ ውስጥ የገባችው ሲኖዶሱ ቀኖናውን በመጣስ የጎሣዊ ፋሽስቶች የብሔር ብሔረሰቦች ፖለቲካ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ተቋማት ውስጥ እንዲቋቋም በማድረጉ ነው። ሲኖዶሱ ለሺህ ዓመታት የቆየውን የቤተክርስቲያኗን የመሾሚያ መስፈርት የማያሟሉ የኦሮሙማ ፋሽስት አገልጋዮችን በማስገባት (ከቀሲስ በላይ ጀምሮ እስከ ሳዊሮስ ድረስ) በሲኖዶሱ ውስጥና በተለያዩ የቤተክህነት የኃላፊነት ቦታዎች ተሰግስገው ቤተክርስቲያኗ ከውስጥ እንድትበረበር አድርጓል ።
ከዚህም አልፎ ሲኖዶሱ በሁለት አጋጣሚዎች ምእመናኑን ለእርድ ሜዳ ላይ ጥሎ ከዘረኛው አብይ ጋር ተስማምቷል ። ምእመናኑ ሐይማኖቱን ከጎሳዊ ፋሽስቶች እንዲከላከል ሲኖዶሱ አነሳስቶ፣ ምእመናኑ ለሃይማኖቱ ለመታገል በቆራጥነት በተነሳበት በወሳኙ ሰዓት ያለምንም ውጤት ትግሉን እንዲያቆም በማዘዝ፣ በጎሳዊ ፋሽስቱ አብይ አህመድ እንዲጨፈጨፋ አድርጓል። የመጀመሪያው በ2012—2013 ዓም ሲሆን ፣ ሁለተኛው ደግሞ በያዝነው 2015 ዓም ነው። በሁለቱም ጊዜ ሲኖዶሱ አማኞቹን ሜዳ ላይ አፍስሶ የአብይ አህመድን ትእዛዝ ፈፀመ። እነዚህ የምእመናኑን ቅስም የሰበሩ ፖለቲካዊ ትእዛዞች እነ አብይ አህመድ በሕዝቡ ላይ ፋሽስታዊ በትራቸውን እያሳረፉበት እንዳይመክት አድርገውታል ። የአማራውን የህልውና ትግል በተመለከተ ሲኖዶሱ ውስጥ ያሉ አማራ ጳጳሶች ወለም ዘለም ሳይሉ ትግላችንን እንደሚደግፉ እንጠብቃለን። ቢያንስ ብአዴናዊ አደናቃፊዎች ከመሆን መቆጠብ አለባቸው።
በተለይ ከሁለተኛው ክህደት በኋላ እነ አብይ አህመድ የፈሪ ዱላቸውን አንስተው በድፍረትና በግልፅ መጨፍጨፍ ጀመሩ። ሸገር በተባለው አካባቢ ወደ 112 000 ቤቶችን በማፍረስ ገሳዊ ፋሽስቶቹ „ሕገወጡን ደሃ ሕጋዊ ደሃ" አድርገነዋል በማለት ከ440000 ተፈናቃዮች ላይ በሚድያ ተሳለቁ። የአማራ ክልል የሚባለውን አካባቢ ወረሩ ። የ6 መቶ ዓመቱ የደብረ ኤልያስ ገዳም ሲወድምና ምእመናን ሲጨፈጨፉ ሲኖዶሱ ድርጊቱን ሳያወግዝ የጉዳቱን መጠን ለመመዝገብ አንድ ቡድን ላከ። ከዚያ ውጭ ያደረገው ነገር የለም። ለነዚህ ከባድ ወንጀሎች መፈፀም ሲኖዶሱ ምእመናኑ ተቃውሞውን እንዳይቀጥል ያስተላለፋቸው ሁለቱ የክህደት ትእዛዞች ወሳኝ አስተዋፅኦ አድርገዋል ። ዛሬ ቤተክርስቲያናችን በጎሰዊ ፋሽስት ወሮበሎች እየተከፈፋለች፣ እየተዋረደች፣ እየተመዘበረችም ነው። የሲኖዶሱም ከሐዋራያነት ወደ ጎሣዊ ፋሽስቶች አገልጋይነት የሄደበት ጉዞ ይሄንን ይመስላል ።
ሲኖዶሱ የሄደበት አካሄድ በናዚዎች አገዛዝ ሥር ከነበሩት የጀርመን ቤተእምነቶች አካሄድ ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ እዚህ በአጭሩ እናንሳው። ሒትለር ሥልጣን ላይ እንደወጣ ከጀርመን ቤተክርስቲያናት በኩል የሚመጣበትን ጠንካራ ተቃውሞ በማወቁ ቤተክርስቲያናቱን ለመቆጣጠር ወሰነ ። የኢቫንጀሊካል ቤተክረሰቲያንን በተመለከተ፣ የቤተክርስቲያኗ አወቃቀር ጥብቅ ስለአልነበረና (Landeskirchen) እርስ በርሳቸውም የማይስማሙ፣ ውዝግብ የበዛባቸው ስለነበሩ ሒትለር የራሱን ሰዎች በማሰረግ የቤተክርስቲያኒቱን ቁንጮ ጨምሮ ለመቆጣጠር ቻለ። ወዲያው „ቄሶች መሆን የሚፈቀድላቸው ከአርየር(Arier) ዘር ለሆኑ ብቻ ነው(Arierpragraphen) የሚለው ደንብ ወጣ። በዚህም ብዙ ቄሶች ተባረሩ ታሰሩ።

የካቶሊክ ቤተክርስቲያንን በተመለከተ የሒትለር አካሄደ ለየት ያለ ነበር። ወደ መጀመሪያው ሒትለር „ ሁለቱም ቤተእምነቶች ጀርመናዊነትን ዘለቄታዊ ለማድረግ ትልቅ ጠቀሜታ አላቸው" በማለት ሰለአሞጋገሳቸው ካቶሊኮችም ከተቃውሟቸው ለዘብ ማለት ጀመሩ። ከዚያም የሒትለር አገዛዝ ከቫቲካን ጋር Reichskonkordat በመባል የሚታወቀውን ስምምነት በ1933 ዓም ተፈራረሙ ። በዝህም ስምምነት መሠረት የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ያለመንግሥት ጣልቃገብነት አረሷን እንድታስተዳድር ነበር። ሆኖም ትንሽ ቆይቶ ሂትለር ስምምነቱን በመጣስ ካቶሊኮችን ማሳደድ፣ ማሰር ጀመረ።
ሁለቱም ቤተክርስቲያኖች ሙሉ በሙሉ በሒትለር ቁጥጥር ሥር ወደቁ። ዛሬም የኢትዮጵያ ቤተእምነቶች በጎሣዊ ፋሽስቶቹ እጅ ወድቀዋል።
ከፋሽስት ጋር ለማቻቻል መሞከር ጥፋትን፣ ለፋሽስት ተገዥነትን ያመጣል። በሲኖዶሱም ላይ እያየን ያለነው ይሄንኑ ነው። ሲኖዶሱ የቤተክርስቲያኗን ቀኖና ወደጎን አድርጎ የጎሳዊ ፋሽስቶች ፖለቲካ እየተገበረ ነው። ይሄ ደሞ ከቤተክርስቲያን አስተምህሮ ጋር ይቃረናል ። በህልውና ትግል ውስጥ በሚገኘው አማራ ዘንድ በምንም መስፈርት ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም። ሲኖዶሱ የአብይንና የትሕንግን ፖለቲካ እያራመደ ነውና።

**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቀኖናዋና ዶግማዋ ተጠብቀው ለዘላለም ትኑር!!!!**